16ኛ ዓመት ቁጥር 28
16th Year No.28

ባሕር ዳር ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም
Bahir Dar November 22, 2011

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ *1324*
ያንዱ ዋጋ ብር 2.60
Unit price 2.60

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር190 /2003 ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤክስሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

## Contents

**Proclamation No.190 /2011**

**A Proclamation Issued to Amend the Amhara National Regional State ExiseTax proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 190 /2003 ዓ.ም

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤክስሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በሥራ ላይ ያለውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996ዓ/ም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ እና /11/ ድንጋጌዎች መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 190 /2003 ዓ/ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## Proclamation No.190 /2011

### The Amhara National Regional State Excise Tax proclamation Amendment Proclamation

Whereas, it has become necessary to amend the Excise Tax Proclamation No. 103/2003, which is in effect in the Amhara National Regional State ;

Now, therefore; the Council of the Amhara National Region, in accordance with the Powers vested with it under Sub-Article 3/1 and /11/ of Article 49 of the Revised Constitution of the Region, hereby proclaims as follows

**1.Short Title**

This Proclamation may be cited as “The Amhara National Regional State Excise Tax Proclamation Amendment Proclamation No. 190 /2011.”

## 2. ማሻሻያ

በስራ ላይ ያለዉ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996 ዓ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ተተክቷል።"ለ. ታክሱን በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃ የሚያሳይ መግለጫ ከባለሥልጣኑ በሚሰጠው ቅጽ ላይ ሞልቶ በየ30 ቀን ውስጥ ለባለሥልጣኑ በግንባር ቀርቦ ወይም በባለሥልጣኑ በሚወክለው ሶስተኛ ወገን በኩል ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወደያውኑ ገቢ ማድረግ አለበት።

ለ/ የአዋጁ አንቀጽ 17 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 17 ተተክቷል።

### 17. መቀጫን ስለማንሳት

1. ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚነሳው መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም።

ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ /2/ ውስጥ ''የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ'' ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ ''ወይም ይግባኝ ካላቀረበ " ተብሎ ተጨምሯል።

መ/ በአዋጁ አንቀጽ 27 ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /4/ ተጨምሯል።

## 2. Amendment

The Excise Tax Proclamation No.103/ 2003 is hereby amended as follows:

a. Sub- article (b) of article 8 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article (b): "Submit every 30 days, in a form which shall be applied by the authority, a declaration containing such information as may be necessary for proper collection of the tax and simultaneously pay the tax to the tax authority or through financial institution delegated by the tax authority or through electronic filing and payment system."

b. Article 17 of the proclamation is repealed and replaced by the following new article 17:

### 17. Waiver of penalty

1. Administrative penalties may be waived in accordance with directives issued by the tax Authority.
2. The administrative penalty to be waived in accordance with sub article (1) of this article may not include the interest computed in accordance with article 20 of this proclamation.

c. the Phrase "if fails to appeal" is added after the phrase "in default of paying additional tax required of him" in sub-article 2 of article 18.

d. The following new sub- article 4 is added under article 27 of the proclamation:

/4/ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለ በቂ ምክንያት አንድን ጉዳይ በማጓተት በግብር ከፋዩ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሄር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

## 3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ- ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም
አያሌዉ ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዘዳንት

"4.the Authorities officer shall be held responsible for any damage caused to a tax payer by delaying, with out any good cause, the performance of his/her duty, such employee in addition to being held liable for the damages, shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years."

## 3. Effective Date

This proclamation shall enter in to force as of its publication in the Zikr- Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir- Dar
This 22th day of November 22, 2011
Ayalew Gobezie
President of the Amhara National Region